

# ድክመቶችና ስህተቶች፤ የኢትዮጵያና ኤርትራ የመወሃድ ሂደት ችግሮችና: ያሁኑ ሁኔታ

ተስፋጽዮን መድሀኔ (ፐሮፌሰር)

ብረመን ዩኒቨርሲቲ፣ ጀርመን

2ኛው የኢትዮጵያና ኤርትራ ወዳጅነት ኮንፈረንስ

ሳን ሆዘ፤ ካሊፎርንያ

ማርች 12-14፡ 2010

# ድክመቶችና ስህተቶች፤
# የኢትዮጵያና ኤርትራ የመወሃድ ሂደት
# ችግሮችና: ያሁኑ ሁኔታ

**ተስፋጽዮን መድሀኔ (ፕሮፌሰር)**

**ብረመን ዩኒቨርሲቲ፣ ጀርመን**

አስቀድሜ ጊዜያቸውንና አቅማቸውን መስዋእት አድርገው ይህንን ኮንፈረንስ ላዘጋጁት እህቶችና ወንድሞች ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ቀጥየም ይህን ያህል ህዝብ በዚህ ኮንፈረንስ ለመሳተፍ በመምጣቱ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። የዚህ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎች በሙሉ የኢትዮጵያና የኤርትራ ዝምድናን ለሚመለከት ጉዳይ ከፍ ያለ ግምት የምትሰጡት መሆናችሁ ይገባኛልና በጣም አመሰግናችሁዋለሁ።

ዛሬ አጠር ባለ መልኩ የማስተላልፈው መልእክት አምና በዚህ ቦታ ላቀረብኩት ገለጻ ተከታይ ክፍል ነው ለማለት ይቻላል፤ አምና "ኢትዮጵያና ኤርትራ፣ ከየት ወደየት?" በሚል ርእስ በተዘጋጀ ውይይት የሁለቱ አገሮች ዝምድና -አሁን ባለው ሁኔታ- አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ በሁዋላ በሚቋቋመው ኮንፌዴሬሽን ነው ሊጀምር የሚችለው ብዬ ለማስረዳት መሞከሬ ይታወሳል። በንግግሬ መደምደሚያ ላይ የሁለቱ አገሮች ልሂቃን በተቻለ መጠን የመዋሃድ (የመግባባት) መንፈስ በህብረተሰቦቻችን መካከል ይሰፍን ዘንድ ጥረት እንዲያደርጉ ለማስታወስ ሞክሬ ነበር። ዛሬ በማስተላልፈው መልእክቴ ላይ ይህንን ነጥብ ትንሽ ዘርዘር ባለ መልኩ እዳስሰዋለሁ።

**፩**

የአምናው ኮንፈረንስ ከተጠናቀቀ በሁዋላ በጉዳዩ ላይ ብዙ ሰው ከመወያየቱም በላይ በርካታ ሃሳቦች ቀርበው ነበር። ለኢትዮጵያና ኤርትራ ቀና ያስባሉ ብዬ የገመትኩዋቸው እህቶችና ወንድሞች ሃሳቤን በበጎ ጐኑ ተቀበሉት። ይሁንና ዓላማቸውና መንፈሳቸው ገንቢ ሆኖ እያለ የችግሮቻችንን እና የዕንቅፋቶቻችንን ባህርያት ገና በሚያስፈልገው መጠን ያልተረዱ ወገኖች አሉ። ስለሆነም ከነዚህ ወገኖች ጋር በተደጋጋሚ መወያየትና መግባባት ያሻል።

ከዚህ ግንዛቤ ተነስቼ በ1940ዎቹ መጀመርያ ዓመታት የተጀመረው የሁለቱ አገሮች የውህደት ሂደት ደረጃ በደረጃ ወይም በየመድረኩ እንዴት እንደተበላሸና እስከ መገንጠል ደረጃ ለምን እንደደረሰ ማጥናቱና ማስተዋሉ፤ ባህላዊ አመለካከታችን ወይም ባህላዊ ዕሴቶቻችን ደግሞ በሂደቱ መበላሸት ምን ሚና እንደነበራቸው ለስሜት ሳይሸነፉ መመርመር ያስፈልጋል ብዬ ደመደምኩ።

የዚህ ምርምር ዓላማ ባለፉት መድረኮች ለፈጸምናቸው ስህተቶች መሰረታዊ መግለጫዎች ምን እንደሆኑ ለይቶ በማውጣት ባሁኑ ጊዜ ደግሞ እነዚያ ስህተቶችና ድክመቶች በምን መልክ እየተገለጹ መሆናቸውን በመረዳት አካሄዳችንን እንድናስተካክልና፡ የሁለቱን ህዝቦች ነጻነት፡ ወንድማማችነት፡ ሰላምና ብልጽግናን ለማረጋገጥ እንድንበቃ ነው።

ይህንን ምርምር ስናካሂድ ብዙ ጥያቄዎች እግረ-መንገዳቸውን ይነሳሉ። ጣልያን ተሸንፎ ኤርትራንና ሌሎቹን ቅኝ ግዛቶች ከተነጠቀ በሁዋላ ያገሪቱን መጪ ዕድል በተመለከተ ኤርትራውያን “ማሕበር ፍቕሪ ሃገር” በሚል መጠሪያ ተደራጅተው መንቀሳቀስ ጀመሩ። በአንድ ወቅት ብዙዎቹ፡ የተለያዩ የኤርትራ ብሄረ-ሰቦች መብቶች እንዲጠበቁ ዋስትና የሚሆን ቅድመ-ሁኔታን የጨመረ ህብረት ከኢትዮጵያ ጋር በሚለው አቋም ተግባቡ። የህብረቱን ሂደት የሚፈታተን ንቅናቄ ለምን ተነሳ? ፌዴሬሽን የሚለው መፍትሄ ለምን እና እንዴት መጣ? የአጼ ሃይለ ስላሴ መንግስትና ኤርትራ የነበሩት ተባባሪዎቹ ከመጀመሪያ አንስተው ፌዴሬሽኑን መሸርሸርና ማዳከም ተያያዙት። ለምንድነው ይህ የሆነው? ወይም ይህ ተግባር በምን ዓይነት አመለካከት ወይም ዕሴት ይገለጻል? በመሰረቱም ፌዴሬሽኑ በመሸርሸሩና በመፍረሱ በተጨባጭ ኤርትራውያን ምንድነው የጐደለባቸው? የትኛውን መብታቸውን አጡ? የዚህ ሁሉ ውጤት የሆነው ቅሬታ በምን መልኩ ተንጸባረቀ? በፌዴሬሽኑ መሸርሸርና መፍረስ ቅር ተሰኝተው ጀብሃን የተቀላቀሉት ዜጎች አብዛኛዎቹ እስላሞች የሆኑት በምን ምክንያት ነው? የኤርትራን ንቅናቄ በእውኑ ዓረብ አገሮች ያነሳሱት ወይም ያስጀመሩት ነበር? ንቅናቄው እያደገ፡ ችግሮቹ ደግሞ እየተባባሱ ሲሄዱ የአጼ ሃይለስላሴ መንግስት ለምን ተግባራዊ መፍትሄ አላፈላለገም? ደርግ ስልጣን ሲይዝ ምን ሊያደርግ ይችል ነበር? የኤርትራ ጥያቄ ከሌሎች ብሄር ብሄረ-ሰቦች ጥያቄ የሚለይበት ረገድ እንደነበረ ለምን አላጤነም? የኤርትራ ንቅናቄ ከመገንጠል በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበረውም? አማራጮቹ ለምን ለኤርትራ ህዝብ ተነፈጉት?

አሁን ያለው ሁኔታ የተወሳሰበ ነው። ኤርትራ ውስጥ፡ ወይም በኤርትራ ማህበረሰብ ውስጥ፡ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት (ከሌሎች አገሮች ጋር ያላት ግንኙነት ዓይነት ካልሆነ በስተቀር!) የማይፈልግ ወገን አለ። በሌላው በኩል ደግሞ የኮንፌዴሬሽን ሃሳብ የሚደግፍ አለ። ለዘዴ -ማለት ለመላ- ብሎ ፌዴሬሽንም እንቀበላለን የሚል -አቶ ኢሳያስ አፍወርቅም የደገፉታል የሚባለው- ወገንም አንዳንዴ ብቅ ይላል። በኢትዮጵያውያን በኩልም እንዲሁ ከኤርትራ ጋር ግንኙነት የማይፈልግ አለ። የኮንፌዴሬሽን ሃሳብ የሚደግፍም፡ የማይደግፍም አለ። አንዳንዱም፡ የአቶ ኢሳያስን ቃል አምኖ፡ በአቶ ኢሳያስ ትብብር ፌዴሬሽን ይቋቋማል ብሎ የሚጠብቅ አለ። ይህ ሁሉ ምንን ያመለክታል? ስለ አስተሳሰባችንስ ምን የሚጠቁመው ነገር አለው?

አሁን ያለው ሁኔታም ያው ከ40ዎቹ አንስቶ ሲያደናቅፈን በኖረው አመለካከት ወይም ርዕዮተ-ዓለም የተለወሰ ነው። መፍትሄው ምንድን ነው? በኢትዮጵያና ኤርትራ መሃከል ፈደራላውነት (ፈደራሊዝም) እንዲዋቀር እንዲጐለብትና እንዲያድግ የልሂቁ ሚና ምንድን ነው? የመግባባት ወይም የመዋሃድ መንፈስ እንዲሰፍን ልሂቆቹ ምን ማድረግ አለባቸው? እርስ በርሳችን መግባባት አለብን ሲባል ሁልጊዜ እንሰማለን። ይህ ግን በእውነት ምን ማለት ነው?

እነዚህ ሁሉ መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች ናቸው። ሌሎች ጥያቄዎችም አሉ። ዛሬ በዚሁ ኮንፈረንስ ሁሉንም በዝርዝር ልንመልስ ጊዜው ባይፈቅድልንም፡ ዋና ዋናዎቹን ጥያቄዎች አጠር-አጠር አድርገን ለማየት እንሞክራለን።

፪

በዚሁ ጊዜ አንዳንድ ታዛቢዎችና ተንታኞች የፖለቲካ ችግሮቻችን ዋና መንስዔ የማርክሰ-ሌኒንነት ውርስ የሆነው ስልጣን ለብቻ ጠቅልሎ የመያዝ ባህርይ ወይም ዝንባሌ ነው ይላሉ። ለምሳሌ ፕሮፌሰር ያዕቆብ ሃይለማርያም ባለፈው ታህሳስ ወር በታተመ ጽሁፍ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ባለፉት 30 ዓመታት ልዩነቶቻቸውን በመግባባት ፈትተው ሊጓዙ አልቻሉም፣ የዚህ ችግርና ውድቀት ምክንያትም የአጀማመራቸው ሂደት በማርክሰ-ሌኒንነት የተቀረጸ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ

ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። ከዚህ ጋር በማያያዝም የኛን ትውልድ፡ አቶ መለስ ዜናዊ የሚመሩት ኢህአደግን ጨምሮ፡ ያሳደገ ማርክሰ-ለኒኒዝም፡ ጨዋነት እና በድርድር ስምምነት ላይ መድረስ፡ እምብዛም የማይፈቅድ አመለካከት መሆኑን ይገልጻሉ።

ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊም በበኩላቸው የፕሮፌሰር ያዕቆብን ጽሁፍ አስመልክተው "ስለማርክስነታቸው" -"ምን አይነት ማርክስነት ያነቡ" ወይም "በድሮው ፓርቲያቸው ይተገብሩ እንደነበረ"- አስተያየት ልሰጥ አልችልም በማለት ማንኳሰስ በተስተዋለበት ቃና ተናግረዋል።

ፕሮፌሰር ያዕቆብ በምሁርነታቸው ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ዕድገት ከተማሪነት ጊዜ አንስተው እስካሁን ባበረከቱት አስተዋጽኦ የሚከበሩ ሰው ናቸው። ስለ ማርክሰ-ሌኒናዊ ያሰተሳሰብ ስረ-መሰረታችን ያቀረቡት አስተያየት ግን፡ በኔ አመለካከት፡ በከፊሉ ወይም በተወሰነ ገጽታ ብቻ ነው ትክክል የሚሆነው። እርግጥ ነው፡ በ60ዎቹና በ70ዎቹ በስመ ማርክስነት የተማሪና ያንዳንድ ምሁራን ንቅናቄዎች ሲጓዙ ነበር። ነገር ግን በእውነተኛ አመለካከትና ይዘት፡ የንቅናቄዎቹ መሪዎች ይሁኑ አባላት፡ ምናልባት በጣም ጥቂት ካልሆኑ በስተቀር፡ ማርክሳዊ አልነበሩም። እንዲያውም በዚያን ጊዜ ተማሪው: ባገር ተቆርቋሪነቱ እና ለመስዋእት በነበረዉ ዝግጁነት የሚከበር ቢሆንም፡ ስለማርክስነት በቂ ዕውቀት ሳይኖረው ነው ማርክሳዊ ነኝ ብሎ አምኖ በስመ ማርክስነት ብዙ ስህተት የፈጸመው። በዚያን ጊዜ ጨዋነት (civility) አልነበረም፤ አሁንም እምብዛም የለም፤ በዚያን ጊዜ ኢ-ዲሞክራሲያዊ ፖሊሲዎችና አካሄዶች ነበሩ፤ አሁንም አሉ። እነዚህ ሁሉ በስመ ማርክስነት ቢካሄዱም በርግጥ ማርክስነትን የሚያንጸባርቁና በማርክሳዊ ርዕዮተ-ዓለም ላይ የተመሰረቱ አልነበሩም፤ አሁን እየተካሄዱ ያሉት ኢዲሞክራሲያዊ ፖሊሲዎችም -የነአቶ መለስ ዜናዊ አብዮታዊ ዲሞክራሲን ጨምሮ- የሶሺያሊስት ስርዓቶች የሚመስል አቀራረብና ዘይቤ ቢጠቀሙም፡ በውነቱ በአላማ ይዘት ይሁን በመንፈስ ለማርክስነት ታማኝ የሆኑ፤ ወይም ባጠቃላይ ማርክስነትን የሚያንጸባርቁ አይደሉም።

እዚህ ጋር አንድ ነጥብ መጥቀስ እወዳለሁ። ይህንን ጉዳይ ሳነሳ ለማርክሰ-ሌኒንነት ጥብቅና ለመቆም ብዬ አይደለም። ነገር ግን ችግሮቻችን ከ60ዎቹ በፊት የተነሱ በመሆናቸው፤ ያጠፉትና ስህተት የፈጸሙትም ማርክሲስት ነን ባዮች ብቻ ሳይሆኑ፡ ማርክሲስት ያልሆኑና ጸረ-ማርክሲስት አቋም የነበራቸውም ጭምር ስለሆኑ፡ ያስተሳሰብ ችግሮቻችን መንስኤ ወይም መግለጫ ምን እንደሆነ ለመረዳት ከማርክሳዊ ርዕዮተ-ዓለም ውጪ በሆኑ ዘርፎች ማፈላለግ እንዳለብን ለማሳየት ነው።

ከፕሮፌሰር ያዕቆብ አስተያየት ጋር፡ በተወሰነም ቢሆን፡ የሚመሳሰል አስተያየት የሰጡት ሌላው ምሁር ዕውቁ አሜሪካዊ ሶሲዮሎጂስት ፕሮፌሰር ዶናለድ ለቪን ናቸው። ኢትዮጵያ በቅርብ ታሪኳ ያጋጠሙ ዕድሎችን ለምን ሳትጠቀምባቸው እንደቀረች በተነተኑበት አንቀጽ ከችግሮቹ አንዱ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በማርክሰ-ሌኒንነት መማረካቸው መኖሩን ገልጸው፡ ይህ መማረክ ካስከተላቸው ውጤቶች አንዱ ምሁራኖቹ "የማረክሲስቶቹ ***ማኒኪያዊ አመለካከት***" መያዛቸው ነው ይላሉ። ከፕሮፌሰር ለቪን አሰተያየት ጋር ሙሉ በሙሉ አልሰማማም፤ ሆኖም ግን አርሳቸው የተጠቀሙት "**ማኒኪያዊ አመለካክት**" የሚል ሓረግ ያሰተሳሰብ ችግራችንን ለመረዳት የሚያግዝ: መመርመር ያለበት ጠለቅ ያለ ትርጉም ያዘለ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

## ፫

ማኒከዪዝም ፍጹማዊ የሆነ፡ ሁሉንም ነገር ከሁለት ተጻራሪ መርሆዎች ወይም ምርጫዎች አኳያ የሚያይ አስተሳሰብ ነው። ድሮ፡ ማለት በ3ኛው ክፍለ-ዘመን፡ እንደ

ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ቢጀምርም፡ አሁን ማኒከዪዝም ሲባል ማንኛውንም ሁኔታ ለሁለት የማይታረቁ ተጻራሪ ሃይሎች -አንዱ በጎ፤ ሌላው መጥፎ- እንደተከፈለ አድርጎ የሚመለከት እይታ ማለት ነው። ሁሉም ነገር ከሁለቱ አንዱ ተብሎ ይገለጻል። ለምሳሌ፡ ጥሩና መቅሰፍት፤ ነጭና ጥቁር፤ መጥፋት ያለበት ጠላት እና ወገን የሆነ ወዳጅ ወዘተ ወዘተ። ከሁለቱ አንዱ መሆን ብቻ ነው የሚቻለው። ሶስተኛ፡ ማለት አሻሚ ወይም መሀከለኛ ሁኔታ ሊኖር አይችልም።

በባህላችን እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ ያለ መሆኑ እውነት ቢሆንም እኔ እስከማውቀው ድረስ ማኒከይዝም ተብሎ እንደ ጽንሰ-ሃሳብ የታወቀና የሚጠራ አይደለም። ይህንን ግንዛቤ ወይም ጽንሰ-ሃሳብ በምሁራዊ ደረጃ ተገልጾ ያየሁት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና ዲፓርትመንት እና በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መምህር የሆኑት ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ በጻፉት በየካቲት 2001 በ**አዲስ ነገር** ጋዜጣ በታተመው አንቀጽ ነው። ዶ/ር አሰፋ እንደጻፉት፡

> *"ከባህላዊ አመለካከት አኳያ እስከዛሬ ያልተቸነው እና ለብዙ ዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው (የኖረው) 'የሴማውያን ዕይታ' ተብሎ የሚታወቀውን የማኒኪያን አስተሳሰብ ነው። ማኒከይዝም 'ዓለም ከጥንት ፍጥረት ጀምሮ በሁለት ተጻራሪ እና ተፋላሚ ሃይሎች መካከል ተወጥራ ትገኛለች'፡ ብሎ ስለሚያምን ሁሉንም ነገር የሚመለከተው በሁለት አጽናፎች ላይ ብቻ ተወስኖ ነው። እነዚህም ብርሃንና ጨለማ፤ በጎና ክፉ፤ አጥፊና ጠፊ ሲሆኑ፡ እነዚህ ሁለት አጽናፎች የሚጋጩበት እና በአጠቃላይ ተቃርኖ የሰፈነባት ዓለም ውስጥ እንዳለን ያቀርባል፤ በሁለቱ አጽናፎች ያለ ሶስተኛ እውነታ ሊኖር አይችልም ብሎ ያምናል። ይህ አይነቱ አመለካከት በአንድ ማህበረ-ሰብ ውስጥ የሚነሱ ባህላዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ከሁለት አጽናፎች ውጭ ለመመልከት አይችልም። ስለሆነም፡ይህ አይነቱ ግንዛቤ በባህል በስነ-ምግባር፡ እና በፖለቲካ ህይወት ዙርያ (ላይ) ተጽእኖውን ያሳርፋል።"*

ማኒከዪዝም በነዚህ ሁሉ ዙሪያዎች የሚነሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚጠቀመው አቀራረብ ቀላል ነው። ሁሉም ነገር ነጭ ወይም ጥቁር፤ በጎ ወይም ክፉ፡ ወዳጅ ወይም ጠላት ነው። የተወሳሰበና ለመፍረድ ወይም ለመወሰን የሚያስቸግር ጥያቄ አይኖርም። ይህ ታዲያ ችግር ለመፍታት አይረዳም። እንዲያውም ቆየት ብለን ስለ ኢትዮጵያና ኤርትራ የቅርብ የፖለቲካ ታሪክ ስንወያይ እንደምናየው በመጨረሻ ነገሮችን ያበላሻል።

በማኒከያዊ አስተሳሰብ አሻሚ ነገር ስለሌለ መደራደርና ስምምነት ላይ መድረስ አይታሰብም። አንዱ -ማለት በጎው- ወይም ሌላው -ማለት መጥፎው- ያሸንፋል። መቻቻል የሚባል ነገር ቦታ አይኖረውም።

የዛሬው አጀንዳችን ወይም የውይይታችን አርእስት ፖለቲካዊ በመሆኑ፡ ማኒከዪዝም በፖለቲካ ረገድ ምን መልክ እንዳለው፡ ምን ውጤት እንደሚያስከትል፡ እና ምን ችግር እንደሚፈጥር መጥቀስ አስፈላጊ ነው።

ማኒኪያዊ ፖለቲካ ልዩነትን አይቀበልም። አንዱ ወገን ራሱን እንደ ፍጹም ትክክለኛ ቆጥሮ ሌላውን ወገን ደግሞ ፍጹም የተሳሳተ ወይም መጥፎ አድርጎ ያየዋል። ስልጣን መጋራት ወይም ተደራድሮ ሁሉንም ወገን የሚያረካ መፍትሄ ማፈላለግ ለማኒኪያዊ ፖለቲካ የሚጥም አይደለም። ውድድር ቢኖር ድሉ የራሱ ብቻ እንዲሆን ይፈልጋል፤ ይጥራል፤ ቢቀናውም ያደርጋል። ለምሳሌ የብሄራዊ አንድነት መንግስት የሚባል ገንቢ ሃሳብ ማኒኪያዊ አመለካከት ላለው አካል አይስማማውም። ዶ/ር ዳኛቸው እንዳሉት፡

> *"የፖለቲካ ገጽታውን እንደምሳሌ ብንወስድ ማኪከዪዝም ፍጹማዊ የፖለቲካ ዕሴት* (value)፡ *አንድ ወጥ የፖለቲካ ትንታኔ፡ አንድ አይነት የታሪክ ዕይታ ብቻ የሚያስተናግድ አስተሳሰብ ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሰረት በፓርቲዎች መካከል የሚነሳ ውድድር ውጤቱ ምንጊዜም ፍጹማዊ እና ብቸኛ ድል መሆን አለበት።"*

ማኒኪያዊ ፖለቲካ ድሮም ነበር፡ አሁንም አለ። 'የሴማውያን ዕይታ' ተብሎ ቢገለጽም፡ ይህ ያስተሳሰብ ጠባብነት ከጥንታዊ ባህል ውርስ ባልተገላገሉት ታዳጊ ሃገሮች ብቻ ሳይሆን ሰለጠኑ በሚባሉት ህብረተ-ሰቦችም የሚታይ ነው። ለምሳሌ በዚሁ አገር -ማለት በዩናይትድ ስተትስ- እስከ 2008 ዓ. ም. ድረስ ርእሰ-ብሄር የነበሩት ጆርጅ ደብልዩ ቡሽ "ማኒኪያን ፕረዚደንት" ተብለው ይገለጻሉ። ለዚህ አገላለጽ ምክንያት የቡሽ አመለካከት ዓለምን "በሁለት ተጻራሪ እና ተፋላሚ ሃይሎች" በቆመ ሁኔታ ከማየት የመነጨ በመሆኑ ነው። በንግግሮቻቸው እርሳቸው የሚመሩዋት ክፍለ-ዓለም የበጎነት ወገን፡ ሌሎቹ ደግሞ የመቅሰፍት ወይም የሃጢአት ጎራ ናቸው። ቡሽ ደግመው-ደጋግመው *"ወይም ከኛ ጋር ናችሁ፡ ወይም ከሽብርተኞቹ ወገን ናችሁ"* ብለው ተናግረዋል። ባመለካከታቸው አንድ አገር ወይ መንግስት የአሜሪካ ተባባሪ ወይም ታዛዥ ያልሆነ ሽብርተኞችን የሚቃወም ነጻ አካል ሊሆን አይችልም። ወይ የአሜሪካ ተባባሪ፡ ወይ ደግሞ የሽብርተኞች ወገን መሆን ብቻ ነው የሚቻለው በቡሽ አመለካከት።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መጠቀስ ያለበት ነጥብ አለ፡፡ አንድ ማኒኪያዊ አመለካከት ያለው መሪ ወይም ቡድን የኔ አካሄድ ብቻ ነው ትክክለኛው ብሎ በማመኑ ወይም በማሰቡ የሚከተለው ወይም የሚተገብረው ፖሊሲ (የጦርነትን ጨምሮ) ፡ ወይም በአንድ ጉዳይ የያዘው አቋም የተሳሳተና አፍራሽ መሆኑ ግልጽ በሆነበት ጊዜም ፖሊሲውን ወይም አቋሙን አይለውጥም፡፡ ለዚህ ነው አንዳንድ መሪዎች ኪሳራንና ውድቀትን ብቻ የሚያመጣ ፖሊሲ (ጦርነትን ጨምሮ) ዝም ብለው ሲቀጥሉበት የምናየው፡፡

በአህጉራችን አፍሪቃ ያለው የፖለቲካ እውነታ እምብዛም በማኒከዪዝም የተጥለቀለቀ ነው፡፡ እንደያውም በአፍሪቃ ያለው ፖለቲካ በመሰረቱ "ባዶ ወይም ሁሉን" (zero-sum) ተብሎ የሚገለጽ ነው፣ ይህ ማለት፡ አንድ ቡድን (ወይም አንድ አምባገነን) የመንግስትን ስልጣን በሙሉ ይጠቀልላል፣ ሌላው ምንም አያገኝም፡፡ ይህ እንግዲህ እውነተኛው የዝምድና ይዘትን በተመለከተ ነው፣ ካለበለዚያ ለማስመሰል ወይም ለይስሙላ አንዳንድ የዲሞክራሲ መልክ ያላቸው ገጽታዎች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ኬንያን በተመለከተ አንድ ታዛቢ ሲተነትን፡ ያች አገር ገና በ60ዎቹና በ70ዎቹ ከነበረችበት የጕሳ ፖለቲካ አልተላቀቀችም፤ ፖለቲከኞቹ ሁኔታውን የሚመለከቱት ማኒከያዊ ከሆነው "እኛ ኪኩዩዎች እና እነዚያ ኪኩዩ ያልሆኑት" በሚለው እይታ ነው፡ ይላል፡፡

ይህ አደገኛ ነው፡፡ በአንዳንድ ከመጠን ያለፈ ሁኔታማ ማኒኪያዊ አመለካከት ያለው አምባገነናዊ ቡድን *"እኛ እንገዛላን፡ ካለበለዚያ አገሪቱም ትጥፋ"* በሚል አቋም ይደርቃል፡፡

በሱዳንም እንደዚሁ ሁለቱ ተፎካካሪ ቡድኖች ማኒኪያዊ ፖለቲካ እያካሄዱ ነበር፡፡ ካርቱም ያለው ብሄራዊ እስላማዊ ግንባርና ደቡቡን የሚወክል የሱዳን ህዝብ አርነት ግንባር ማኒኪያዊ የሆነ ድል ሲፈልጉ ነበር፡፡ ይህ ማለት የካርቱሙ ግንባር አረባዊት እስላማዊት ሱዳን ሲሻ፣ የደቡቡ ሃይል ደግሞ የተባበረች ዓለማዊትና ዲሞክራሲያዊት ሱዳን ሲፈልጉ ነበር፡፡ ይህ ግን፡ ሁለቱ ወገኖች ማኒኪያዊ በመሆናቸው፡ በጦርነት በማሸነፍ ብቻ ነበር ሊረጋገጥ የሚችለው፡፡ ከሁለቱ ግን ማንኛቸውም በጦርነት ሊያሸንፍ አልቻለም፡፡ የሚሊታሪ እውነታው ማኒኪያዊ መደምደሚያ እንዲቻል አላደረገም፡፡

ስለዚህ፡ ይላል አንድ ተንታኝ፡ ሱዳንን በተመለከተ ተግባራዊ የሆነ መፍትሄ የሚገኘው ሁለት ሉአላዊ አገሮች አብረው ሊኖሩ ከሚያስችል የኮንፌዴሬሽን መዋቅር ነው፡፡ (በሌላ አነጋገር፡ ሰሜንና ደቡብ ሱዳን ይለያዩና ወዲያውኑ በኮንፌዴሬሽን ይተሳሰራሉ፡፡)

አሁን የኛን ባህል በተመለከተ ያለውን ሁኔታ እንመልከት፡፡ አንድ ታዛቢ የኢትዮጵያውያን ባህላዊ (ልምዳዊ) ርዕዮተ-ዓለም ማኒኪያዊ ባህርይ እንዳለው ይገልጻል፡፡ የኤርትራውያኑም እንደዚሁ ነው፡፡ ዋና መለያ ጸባዩ ሁለትነት (duality) መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለውጥ ይሁን ሌላ ህብረተ-ሰብአዊ ሂደት የሚከሰተው በሁለት ተጻራሪ ሃይሎች መካከል በሚካሄደው ትግል ቆሞ በተገመተው ዕውነታ ነው፡፡ ይህንን ማኒኪያዊ አመለካከት በማጠንከር ሃይማኖቶቻችን ትልቅ ሚና እንዳላቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ባህላዊ የትምህርት ተቋማት ለህብረተሰብአዊ ሂደቶቻችን የሚሰጡት (የሚያቀርቡት) መግለጫ በጎና መጥፎ በሆኑት ተጻራሪ መሎኮታዊ ሃይሎች መካከል የሚካሄድን ትግል መሰረት በማድረግ ነው፡፡

በህብረተሰባችን እንደ ጽንሰ-ሃሳብ ተለይቶ እምብዛም የሚታወቅ ባይሆንም፡ ማኒከዪዝም እንደ ተርዕዮ በተጨባጭ የሚስተዋል መሆኑ ግልጽ ነው፤ የሚያስተውሉትም ከተወሳሰበ የህይወት ዕውነታ ጋር የማይጣጣም መሆኑን ይገልጻሉ። ለምሳሌ በዕውቀቱ ስዩም የተባለ ደራሲ "በራሪ ቅጠሎች" በተሰኘው መጽሃፉ "የቅጠል ቤት ታዳሚዎች" ብሎ ስለሚጠራቸው ገጸ-ባህሪዮች (characters) እንዲህ ይላል፡

> *"የቅጠል ቤቱ ታዳሚዎች ሁሉ ለመናገር እንጂ ለመስማት የሚመጡ አይደሉም፡ .......*
>
> *"እነሱ ዘንድ መፍረድ ቀላል ነው። ሲፈርዱ ጥግ እንጂ አማካኝ መኖሩን አያውቁም። ቆላ ካልሆነ ደጋ ነው ይላሉ፤ ወይናደጋ መኖሩን አይረዱም። ብርሃን ካልሆነ ጨለማ ነው ይላሉ፤ ከጨለማ የፈካ፡ ከብርሃን የደበዘዘ ድንግዝግዝ መኖሩን አያውቁም። ንፍር ካልሆነ በራድ ነው ይላሉ፤ ለብታ መኖሩን አያስተውሉም፡፤ ጠላት ካልሆነ ወዳጅ ነው ይላሉ፤ መሃል ሰፋሪን አይቀበሉም።"*

ይህ ትዝብት ማኒከዪዝም በህብረተ-ሰቦቻችን በተለያዩ ዘርፎች ያለ የባህላችን አካል ወይም ያአስተሳሰባችን ባህርይ መሆኑን ነው የሚያመለክተው።

ይህ ማኒኪያዊ አስተሳሰብ የባህላችን አንድ ባህሪ በመሆኑ ባሁኑ ፖለቲካችን ላይም ትልቅ ተጽእኖ ያደርጋል፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው እንዳሉት፡

> *"ይህ የማኒከይዝም አመለካከት በአገራችን ለረጅም ጊዜ ስር ሰዶ የቆየ፣ ባህላዊ መሰረት ያለው ከመሆኑ አኳያ አገራችንን በሚያስተዳድረው ፓርቲ ላይ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚ ፓርቲዎችም ላይ የሚታይ ችግር ነው፡፡"*

በቅርብ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ አንዳንድ ተቃዋሚዎቻቸውን ማኒኪያዊ መንፈስ በሚያንጸባርቅ ቋንቋ ሲያጥላሉ ተሰምተዋል፡፡ ህወሓት የተመሰረተበት 35ኛው ዓመት ባለፈው የካቲት 11 በመቀሌ ከተማ ሲከበር ባደረጉት ንግግር ፓርቲያቸውን እየወደሱ ተቃዋሚዎቻቸውን፡ በተለይ የህወሓት አንጋፋ አባላት የነበሩትን እነ አቶ ስየ አብርሃንና ገብሩ አስራትን የመሳሰሉን ክፉኛ በማቋሸሽ ተናግረዋል፡፡ ራሳቸውንና ድርጅታቸውን በ "***ንቁ ገበሬ***" እየመሰሉ፡ ተቃዋሚዎቻቸውን "***እንክርዳዶች***"፡ "***ገለባዎች***"፡ "***ጭቃ***"፡ "***ርጋፊ***" ሲሉ ገልጸዋቸዋል፡፡ የዚህ አገላለጽ አደገኛነት የታዘበ የማነ ናግሽ የተባለ ጋዜጠኛ መገሩሙን እንደሚከተለው ገልጸዋል፣

*"አቶ መለስ በዚሁ ንግግራቸው ከድርጅታቸው ካምፕ የተለየ ማንም ሰው ጭቃ፣ ርጋፊ፣ ገለባ፣ እንክርዳድ ነው እያሉን ይሆን? እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብስ ከምን ዓይነት የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ጎራ የመነጨ ይሆን?"*

ጋዜጠኛው የማነ ትክክለኛ ጥያቄ አንስቶ ሲያበቃ የአቶ መለስ አባባልን ያስመነጨ ርዕዮተ ዓለም ምን እንደሆነ ሲያመለክት ግን *"ያልበሰለና የኢትዮጵያን ታሪክ ጠንቅቆ ያልተረዳ ለኒናዊ ማርክሳዊ ርዕዮተ ዓለም"* ነው የሚል ይመስላል፡፡ *የፈረደበት ለኒናዊ ማርክሳዊ ርዕዮተ ዓለም*! አቶ መለስ ያንጸባረቁት ርዕዮተ ዓለም ከማርክሲዝም ጋር ዝምድና የለውም፡፡ የተንጸባረቀው አመለካከት ሌላ ሳይሆን ያ መቻቻልን የማይፈቅደው ማኒከዩዝም የሚባለው "የሴማውያን ዕይታ" ነው፡፡ አቶ መለስና ድርጅታቸው ብርሃንንና በጎነትን ሲወክሉ፡ እነ አቶ ስየ ደግሞ ጨለማንና ክፋትን ይወክላሉ፡፡ በተቃዋሚዎች በኩልም፡ እየተሻለ ቢመጣም፡ ዕርቅን የማይፈቅድ ማኒኪያዊ አመለካከት የተስተዋለበት ወቅት ነበር፡፡ ለምሳሌ የ2005ቱ ምርጫ ካስከተለው ቀውስ ጋር በተያያዘ በተቃዋሚው ወገን የነበሩ አንዳንድ ቡድኖች "ዘረኛ ቅስቀሳ" ሲያካሂዱ ማኒኪያዊ መንፈስ የተጫነባቸው መፈክሮች አሰምተዋል፡፡

በዚሁ ጊዜ በኢትዮጵያ ፖለቲካና በኤርትራ ፖለቲካ የዲሞክራስን፡ የብሄርተኝነትን፡ እና የብሄረ-ሰብን ያጠቃለሉ ብዙ አንገብጋቢ ጥያቄዎች አሉ፡፡ የኢትዮጵያና ኤርትራ ዝምድናን በተመለከተም እንደዚሁ ከብዙዎቹ ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ የታሪክ አተረጓጐምን የሚመለከት አለመግባባት አለ ማለት ይቻላል፡፡ በዚሁ አለመግባባት፡ በዚሁ ትግል ከማኒኪያዊ አመለካከት የመነጨ ድክመትና ስህተት በሁሉም በኩል ይታያል፡፡

አምና በዚሁ ስብሰባ እንደገለጽኩት፡ በዚሁ ወቅት ኢትዮጵያና ኤርትራ በአመርቂነት ሊዛመዱ የሚችሉት (አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ በሁዋላ) በኮንፌዴሬሽን ነው፣ ነገር ግን ቆይቼ እንደምገልጸው (አምናም እንዳመለከትኩት) የሁለቱን አገሮች የቅርብ ታሪክ ግምት ውስጥ ያስገባ ክፍት ወይም ታዳጊ ኮንፌዴሬሽን (ሲምፖሊቲያ) ማለቴ ነው፡፡ ይህንን አቋም ለመውሰድ ብዙ ምክንያቶች አሉኝ፡፡ ምክንያቶቹን አምና ገልጫቸዋለሁ፡፡ አሁን ላተኩርበት የምፈልገው ጉዳይ የኢትዮጵያና ኤርትራ አንድነታዊ ሂደት ለምን እንደተበላሸና ኤርትራን እስከ መገንጠል ያደረሱ ድክመቶችና ስህተቶች ምን እንደነበሩ መመርመር ነው፡፡ እነዚህን ድክመቶችና ስህተቶች ስንመረምር በኔ አስተያየት በዚህ ወቅት ሊደረግ የሚቻለው ዝምድና፡ ከፍ እያለ የሚሄድ ቢሆንም መነሻው ከኮንፌዴሬሽን የጠበቀ እንዳልሆነ እናያለን፡፡

፬

ድክመትና ስህተት የታየው ከመጀመርያው፡ ማለት ከ40ዎቹ አንስቶ፡ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በዚያን ጊዜ የነበረውን የሁለቱ አገሮች ሁኔታ በማስታወስ እንጀምር፡፡

የኤርትራ ህዝብ ክርስትያንና እስላም ነው፡፡ በብዛትም ተመጣጣኝ ነው፡፡ በጣልያን ጊዜ ከባርነት ያልተሻለ ዘረኛ አገዛዝ ቢጫንበትም፡ በእንግሊዞች ጊዜ ከሊበራል ስርዓትና መብቶች ጋር ትንሽ ተዋውቆ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የዚያን ጊዜ በንጉሰ-ነገስት የምትገዛ፡ እንዲያውም መንግስትዋ በመልኩም በይዘቱም ከክርስትያናዊ ሃይማኖታዊ አመራርና ቁጥጥር ያልተገላገለ ፊውዳላዊት አገር ነበረች፡፡ ንጉሰ-ነገስቱ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይና የበላይ ጠባቂ ነበሩ፡፡

የኢጣልያ ቅኝ ግዛት አብቅቶ እንግሊዞች ኤርትራን ሲያስተዳድሩ፡ ኤርትራ ምን ትሁን በሚለው ጥያቄ ላይ ህዝቡ ተለያይቶ ነበር፡፡ በሂደት ግን የተለያዩ ቡድኖች አንድ አማካይ ስምምነት ለመድረስ ተቃርበው፣ እንድያውም ደርሰው ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ስምምነቱም የህዝብ መብቶችን የሚያስከብር ዋስትናን የተመለከተ ነበር፡፡ በይዘቱ ዋስትናው በተለይ ለእስላማዊ ማህበረ-ሰቦችና ሊበራል ዕሴቶች - በእንጭጭ ደረጃም ቢሆን - ለነበሯቸው ቡድኖችን ያሳስቡ የነበሩትን ጉዳዮች የሚመለከት ነበር፡፡ ስምምነቱ ይህ ዋስትናን የጨመረ በውል የተመሰረተ አንድነት ከኢትዮጵያ ጋር መቀበል ነበር፡፡

ይህንን ስምምነት ለማጠቃለል በህዳር 1946 ዓ. ም. ቤት-ጊዮርጊስ በሚባለው ከአስመራ ትንሽ ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ ጉባዔ ሲካሄድ አዲስ ነገር ተከሰተ፡፡ በዚያን ጊዜ በኤርትራ የኢትዮጵያ ሊያይዞን ኦፊሰር የነበሩት ኮሎነል ነጋ ሃይለስላሴ እና ኤርትራውያን ተባባሪዎቻቸው ዋስትና ወይም ውል የሚባል ነገር የሌለው ሙሉ ውህደት ከኢትዮጵያ ጋር የሚል አቋም እንዲገፋበት አደረጉ፡፡ ኤርትራውያን ተባባሪዎቹ “ኢትዮጵያ ለኛ አባትም እናትም ናት፤ ዋስትና፡ ውል፡ ቅድመ ሁኔታ የሚባሉ ነገሮች ቦታ የላቸውም'፡ ትክክለኛው አቋም ሙሉ ውህደት ከኢትዮጵያ ጋር ነው” ብለው ድርድሩን አጨናገፉት፡፡ በነዚሁ የተደራጁ ማህበር አንድነት የተባሉ ብረት የታጠቁ ወጣቶችም ዋስትናና ውል ይጠይቁ የነበሩትን አስፈራሩ፤ አንዳንዱም ለህይወታቸው ሰጉ፡፡ ከዚያን ጊዜ አንስቶ ሁኔታው ተበላሸ፡፡ ከውጤቱ አንዱም የራቢጣ አል እስላሚያ መቋቋም ነበር፡፡ ራቢጣ ማለት ቡድን ማለት ነው፡፡

ራቢጣ አል እስላሚያ ከተቋቋመ በሁዋላ ሁኔታው እምብዛም የተወሳሰበ ሆነ፡፡ ራቢጣውና የተለያዩ ብዙ ቡድኖች ነጻነትን ጠየቁ፤ ማሕበር አንድነት ግን በአላማው ጸና፡፡ ተደራድሮ ከስምምነት ለመድረስ የማይፈቅድ ትግል በአንድነት ፈላጊዎችና በነጻነት ጠያቂዎች መሃከል ተካሄደ፡፡ በመጨረሻም ጉዳዩ ለተባበሩት መንግስታት ቀርቦ አንድ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያስተባብር አስታራቂ ወይም ማስማሚያ ሃሳብ ጸደቀ፡፡ አስታራቂ ሃሳቡም ‘ኤርትራ በኢትዮጵያ ሉዓላውነት ስር ራሷን የምስታደዳድር አካል እንድትሆን’ የሚል ነበር፡፡ ይህ ነበር ፌዴሬሽን ተብሎ የተሰየመው፡፡ ፌዴሬሽኑ የመጣው ዋና ምክንያት እስላማዊው ማህበረሰብ ከኢትዮጵያ ጋር ያለ ዋስትና አንድ ከሆንን መብታችን ልንገፈፍ ነው፡ እንዲያውም የበታች ዜጋ ልንሆን ነው ብለው በመስጋታቸው፡ ከክርስትያኖቹም ከኢትዮጵያ ስር ከሆንን ዲሞክራሲያዊ መብቶች አይኖሩንም የሚል ፍርሃት የነበራቸው ስለነበሩ ነው፡፡ ፌዴሬሽኑ እንግዲህ በመሰረቱ ለነዚህ ቡድኖች ዋስትና ነበር፡፡

በዚህ ምክንያት ነው የተባበሩት መንግስታት ኤርትራ የራሷ ሊበራል ዲሞክራስያዊ የሆነ ህገ-መንግስትና የውስጥ አስተዳደር መንግስት ይኖራት ዘንድ የወሰነ፡፡ በህገ-መንግስቱ መሰረት ህዝቡ በሊበራል ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሚከበሩት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች - የፕረስ፡ የንግግር፡ ፖለቲካ ፓርቲዎች የማቋቋም መብቶች ወዘተ.. ተረጋገጡለት፡፡ ኤርትራ ራስ ገዝ ብቻ ብትሆንም የራሷ ባንዴራ፡ የራሷ መንግስታዊ (ኦፊሺያል) ቋንቋዎች -ትግርኛና አረብኛ-፤ የራሷ ፓርላማ፡ ፓርላማው በሚመርጣቸው ጠቅላይ ሚኒስተር (ቺፍ ኤክዘኩቲቭ) እና ሚኒስተሮች የቆመ ፈጻሚ አካል፤ እና የራሷ ፍርድ ቤቶች እንዲኖሯት ሆነ፡፡

የኤርትራ ሊበራል ዲሞክራስያዊ ስርዓት ኢትዮጵያ ከነበረው ፍጹማዊ ንጉሳዊ አገዛዝ በመሰረቱ የተለየ ስለነበረ አንዳንድ ታዛቢዎች ስጋታቸውን ገልጸው ነበር፡፡ ፈደራላውነት ውስብስብ ያለ ነገር ነው፡፡ አንድ ደራሲ ፈደራላውነትን (ፈደራሊዝም) (“the love of complexity”) -ከውስብስብነት ጋር ፍቅር- ብሎ ገልጾታል፡፡ ቀላል አይደለም ለማለት ነው፡፡ ፈደራላውነት ሲባል፡ አምና እነደገለጽኩት፡ በራስ ገዝነትና በጋራ አገዛዝነት (self-rule and shared rule) የቆመ አውታር ነው፡፡ ይህ ውስብስብ ያለ ሁኔታ ለአጼ ሃይለስላሴ ፍጹማዊ ንጉሳዊ አገዛዝ የሚጥም አልነበረም፡፡ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህልም

ጋር ተስማሚ አልነበረም፡፡ ለምሳሌ የኤርትራ ጉዳይ በፌደራሲዮን እንዲፈታ ይወሰናል ሲባል ጊዜ ልዑል ራስ ካሳ *"በአንድ ኢትዮጵያ ላይ ሁለት መንግስታት ተቋቁሞ ሊካሄድ ነው፡፡ ኤርትራውያኖች የራሳቸውን መንግስት አቋቁመው የሚተዳደሩ ከሆነ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ሆኑ የሚባለው በምኑ ነው? እንደዚህስ የመሰለውን ፍርድ መቀበሉ ጥቅሙ ምንድ ነው?"* ብለው እንደነበር አምባሳደር ዘውዴ ረታ "የኤርትራ ጉዳይ" በተሰኘው ዕውቁ መጽሃፋቸው ነግረውናል (ገጽ 303)፡፡

ፌዴሬሽኑ እንደተቋቋመ አጼ ሃይለስላሴና የከበቡዋቸው ወግ አጥባቂዎች ፌዴሬሽኑን የማፍረስ እቅድ እነደነበራቸው፤ አስተዋይና ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በበኩላቸው ፌዴሬሽኑ እንዳይነካ ያሳስቡ እንደነበር ከተለያዩ ምንጮች እንረዳለን፡፡ ተራማጆቹን በተመለከተ እንደ አንጋፋ ምሳሌ የሚጠቀሱት ጸሃፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሃንስ ናቸው፡፡ ጸሀፊ ትእዛዙ *"የወግ አጥባቂዎቹን ያለ ኤርትራ ህዝብ መልካም ፈቃድ ፌዴሬሽኑን አፍርሶ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ሙሉ ለሙሉ የማቀላቀል ዕቅድን ተቃወሙ፡፡ የኤርትራ ራስ ገዝነትን ማዳከም… በመላ የቀረችው ኢትዮጵያ የፖለቲካ ጠንቅ ያስከትላል ብለው"* ሲያስጠነቅቁ እንደነበር መኰንን ተገኝ የተባለ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጻፈው የማስተርስ ቲሲስ ተመልክቷል፡፡

የተፈራው ደረሰ፡፡ ፌዴሬሽኑ ቀስ በቀስ እየተሸረሸረ በመጨረሻም ያአጼው መንግስትና በኤርትራ ፓርላማ ውስጥ የነበሩ ተባባሪዎቹ ባካሄዱት ሴራ ከነጭራሹ ፈረሰ፡፡

እዚህ ጋር አንድ ነገር ልብ እንበል፡፡ ፌዴሬሽን የተባለው የኤርትራና ኢትዮጵያ ዝምድና ሙሉ አንድነት ነበር፡፡ ኤርትራ በዚሁ አገር ባለው ስርዓት እንደነካሊፎርኒያ ወይም ኒውዮርክ **ፌደረትድ ስቴት** አልነበረችም፡፡ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ስር የራሷ የውስጥ አስተዳደር "ሎካል አውቶኖሚ" ብቻ ነው የነበራት፡፡ ይህ ፍፁም አንድነት ነበር፡፡ ነገር ግን ኤርትራ ***'ጠቅላይ ግዛት'*** ካልተባለች ለአባ ጠቅል አንድነት አልነበረምና ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ተደረገ፡፡

ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ኤርትራ 14ኛዋ ጠቅላይ ግዛት ሆነች ሲባል ምን ማለት ነበር? ፌዴሬሽኑ በመፍረሱ ለኤርትራ ህዝብ ምን ነበር የጐደለው? ፌዴሬሽኑ በመፍረሱ ኤርትራውያን የራሳቸው የራስ ገዝ መንግስት እንዳይኖራቸው ሆኑ፤ ራሳቸውን የማስተዳደር መብት ተገፈፉ፤ ባንዴራቸውን ተነጠቁ፤ ኦፊሺያል ቋንቋዎቻቸውን - ትግርኛና አረብኛ- እንዳይጠቀሙ ተከልክለው፡ የአማርኛ ቋንቋ ተጫነባቸው፤ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶቻቸው - የፕረስ፡ የመናገር፡ ፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም፡ ለስልጣን ለመወዳደር የመሳሰሉትን አያሌ መብቶቻቸውን እኮ ነው የተነጠቁት! ባጭሩ ነጻነታቸውና መብቶቻቸው ተወሰዱባቸው፡፡ ይህ ጭቆና ነበር፡፡

የዚህ ውጤት ምን ነበር? ተጨቆንን፡ ተዘመትን ያሉ ቡድኖች የነጻነት ንቅናቄ አስነሱ፡፡ አስቀድሜ እንዳልኩት ፌዴሬሽኑ በተለይም ለእስላማዊው ወገንና ሊበራላዊ እሴት በትንሹም ቢሆን ቀማምሰው ለነበሩ ልሂቃን ዋስትና ነበር፡፡ ፌዴሬሽኑ ሲፈርስ ዋስትናው ጠፋብን ብሎ የበረገገው ይህ አካል ነበር፡፡ ቆይተውም ድሮ አንድነት ይደግፉ ከነበሩትም ሳይቀሩ ንቅናቄውን ተቀላቀሉ፡፡ ንቅናቄው አድጎ ጀብሃ ተፈጠረ፡፡ አባትና እናት ትባል የነበረችው ኢትዮጵያ ጠላት ሆነች፡፡

ኢትዮጵያ አገራችን ናት! ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን፡ ወገኖቻችን ናቸው! ብለው አንድነትን የተቀበሉ ሳይቀሩ እንዴት ጠላት ይሉናል ያሉ ነበሩ፣ እስካሁንም አሉ፡፡ እንዲህ የሚሉ ኢትዮጵያውያን መብቱ የተገፈፈና የተጨቆነ ህዝብ፡ በማንኛውም ህብረተሰብ፡ ጨቋኙን፡ ወገን ይሁን ባዕድ፡ እንደ ጠላት ማየቱ የማይቀር መሆኑን ይረሳሉ፡፡ ዕውቁ ኢትዮጵያዊ ደራሲ፡ ሟቹ አቤ ጉበኛ፡ **አልወለድም** በሚለው መጽሃፉ እንዳለው፣

*"ወንድም ሲሆንና፡ መልካም ሲሰራ እንጂ ክባዕድ የሚለየው፡*
*ነጻነትንና መብትህን ከነሳህ፡ ወገንም ጠላት ነው፡፡"*

ወገን "ወገን" በመሆኑ ብቻ ጠላት ሊሆን አይችልም የሚል ግምት ስህተት ነው፡፡ በሌላው በኩል ደግሞ መብት ገፍፎ ጠላት በመሆኑ ምክንያት ወገን "ወገን" መሆኑ ይቀራል የሚል አስተሳሰብ ስህተት ነው፡፡ ሁለቱ የተሳሳቱ ግምቶች ማኒኪያዊ አመለካከትን ያንጸባርቃሉ ማለት ይቻላል፡፡

ደርግ ስልጣን ከጨበጠ በሁዋላ ይህንን ሁሉ ለማረም ዕድል ነበረው፡፡ በተቃራኒው፡ ደርግ ኤርትራን ከሚመለከት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ነው፡ የጀነራል አማንን መግደል የጨመረ፡ የመጀመርያው፡ በመጨረሻም የራሱን ውድቀት ያስከተለውን፡ ስህተት የፈጸመው፡፡ ስለ ኤርትራ ጉዳይ አማን የነበራቸው ሃሳብ የድሮው ዓይነት "ፌዴሬሽን" እንዲቋቋም ነበር፡፡ ይህ ትክክለኛ መፍትሄ ቢሆንም፡ ደርግ ይህንን አልቀበልም ብሎ በኤርትራ ንቅናቄዎች ላይ የጦርነት ፖሊሲዉን አወጀ፣ በተጨማሪም አማንን እና ሌሎች 59 የድሮ ባለስልጣናትን በመግደል ለወደፊቱ ደርግ ራሱንም አደጋ ላይ የጣለ ቀውስ አስከተለ፡፡

ኤርትራን በተመለከተ ደርግ እንደ አፄው ሁሉ የኤርትራን የተለየ የቅርብ ታሪክና ፖለቲካዊ ትርጉሙን አላጤነም፡፡ ኤርትራን ልክ እንደሌሎቹ ጠቅላይ ግዛቶች አድርጎ በመቁጠር ተንቀሳቀሰ፡፡ የአመለካከቱ ጠባብነት አልፈቀደለትም እንጂ: ደርግ ለኤርትራ የድሮውን "ፌዴሬሽን" መልሶ: ለሌሎቹ ክፍለ ሃገሮች ደግሞ የዚያው ዓይነት ራስ-ገዝነት ሰጥቶ ሁሉንም ተመሳሳይ በማድረግ ምናልባት ችግሩን ለመፍታት በቻለ ነበር፡፡ በስፔይን ባስክን፡ ካታሎኒያንና ሌሎቹን ክፍለ-ሃገራት በተመለከተ እንዲህ ዓይነት ተግባራዊ መፍትሄ ተሳክተዋል፡፡

እነዚህ ስህተቶች፡ በተለይ የአማን መገደል፡ የኤርትራውያንን ልብ አሸፈቱ፡፡ የነጻነት ግንባሮቹ ጠነከሩ፡፡ ከአረብ አገሮች ያገኙት የነበረ እርዳታ በረከተ፡፡ አረቦቹ እና ሌሎቹ ግን እርዳታ ሰጡ እንጂ የኤርትራ ንቅናቄዎችን አላነሳሱም፡፡ እነርሱ እንዳነሳሱዋቸው አድርጎ ማቅረብ ትክክል አይደለም፣ በተጨማሪም ኤርትራውያንን መልሶ ያበሳጫል፡፡

የጦርነትን አካሄድ በተመለከተም ስህተቶች ተፈጽሟል፡፡ ደርግ በተለይ በመጀመሪያ ዓመታቱ የፈጸመው የግፍ አገዳደል ወጣቱን አስበረገገ፡፡ ለምሳሌ በ1975 በአስመራ ከተማ ወጣቶችን በፒያኖ ሽቦ እያነቀ መግደሉ፣ መንደሮችን በቦምብ መደብደቡ፡ ህዝቡን አስደንግጦ ኢትዮጵያ ኤርትራውያንን እንደ ህዝቦችዋ አትቆጥራቸውም ለሚለው ፕሮፓጋንዳ አመቻቸ፡፡

ማኒኪያዊ ከሆነው ጠባብ አመለካከቱ የተነሳ የደርግ መንግስት የኤርትራ ፖለቲካዊ ችግር ምን እንደነበረ በትክክል ወይም በበቂ አልተረዳም፣ ስለዚህም ሊፈታው አልቻለም፡፡ ፖለቲካዊ ችግሩን በተግባራዊነት ሊፈታ አለመቻሉ በሁሉም በኩል ለአደጋ አጋለጠው፡ ለኤርትራ መገንጠልም አስተዋጽኦ ሆነ፡፡

ኤርትራ የተገነጠለችው ግን የአፄውና የደርጉ መንግስታት ስህተቶች በመፈጸማቸው ብቻ አይደለም፡፡ የኤርትራ ቡድኖች ለዚሁ ውጤት ትልቅ አስተዋጽኦ በማድረጋቸውም ጭምር ነው፡፡

## ፩

የኤርትራ ቡድኖች፡ በተለይ ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ)፡ መገንጠልን እንደ ብቸኛ አማራጭ ከሚያደርግ ጠባብ አመለካከት ተነስተው ድርድር የማይፈቅዱ አቋሞች ወሰዱ፡ ለእርቅ እንቅፋት የሚሆኑ ድርጊቶችም ፈጸሙ፡፡ አንዳንድ ምሳሌ ልጥቀስ፣

1. የኤርትራ ቡድኖች፡ በተለይ ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ፡ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት የሚል፡ ሳይንሳዊ መሰረት የሌለው አቋም ያዙ፡፡ ኤርትራ ቅኝ ግዛት ሆነች ከተባለ ለችግሩ መፍትሄ ነጻነት (መገንጠል) ብቻ ነው፡፡ ወይ ቅኝ ገዢው ይወጣል፡ ወይ ቅኝ ግዛቱ ይቀጥላል፡፡ መሃከለኛ ሁኔታ የለም፡፡

2. የኤርትራ ቡድኖች (በተለይ አቶ ኢሳያስ የሚመራው ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ) የኤርትራን ችግር ከሶሺያሊሰት ጐን ተሰልፋ የነበረችውን የደርግ ኢትዮጵያን ለማዳከም ከፈለጉት ሃያላን መንግስታት ስትራተጂ አቀላቅሎ የቀዝቃዛው ጦርነት ማኒኪያዊ ትግል አካል እንዲሆን አደረገው፡፡ በዛው ማኒኪያዊ ትግል የተፈለገው ደርግን ወይም ስርዓቱን መጣል ስለ ነበረ ለዕርቅና ድርድር የማይፈቅድ አቋም ወሰደ፡፡ ለምሳሌ ደርግ ፋሺስት ነው አለ፡፡ ከፋሺስት ጋር ዕርቅ የለም፣ ፋሺስትን እስኪወድቅ ድረስ ትታገለዋለህ እንጂ ሌላ ምርጫ የለህም፡፡

3. ቡድኖቹ፡ በተለይ ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ፡ ብዙ ጊዜ የህዝቦቻችንን ታሪካዊና ባህላዊ ዝምድና በኤርትራውያን (በተለይ በወጣቱ) እንዳይታወቅ ያደርጉ ነበር፡፡ ይህንንም ከመገንጠል በስተቀር ሌላ ምርጫ እንዳይታሰብ ለማድረግ ተገለገሉበት፡፡

4. ኤርትራ በሴራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ቢደረግም ኤርትራውያን ኢትዮጵያ ውስጥ፡ ባጠቃላይ ሲታይ፡ የተከበሩ እንደነበሩ ከመግለጽ ተቆጥበው፡ ኤርትራውያንን እንደተጨቆኑ አድርገው ብቻ አቀረቡ፡፡ ኤርትራውያን ከእጅ ወደ አፍ የሚኖሩ ብቻ ሳይሆኑ ሚኒስትሮች፡ ጀነራሎች፡ የቀናቸው ባለሞያዎች፡ የተሳካላቸው ነጋዴዎች፤ በማህበራዊ መስክም ያልተናቁና ያልተወገዱ እንደነበሩ ከመመስከር ተቆጠቡ፡፡

5. ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ የኢትዮጵያ ወታደሮች በኤርትራ የፈጸሙትን ግፍ ብቻ እየጠቀሰ ራሱ በኢትዮጵያውያን ላይ ግፍ እንዳልፈጸመ ሆኖ ቀረበ፡፡ ለፕሮፓጋንዳና ለዓለም-አቀፍ እርዳታ ብሎ አንዳንድ ምርኮኞችን ደህና አድርጎ ቢንከባከብም፡ ባጠቃላይ በምርኮኞች ላይ ጭካኔ አሳይተዋል፤ አንዳንዱን እንደ ባርያ አሰርተዋል፡፡ ታደሰ ቴለ ሳለቫኖ "አይ ምፅዋ" በተባለው መጽሃፉ እንደገለጸውም በኤርትራውያን ሬሳና በኢትዮጵያውያን ሬሳ መሀከልም አድልዎ ፈጽሟል፡፡

6. በግንቦት 1991 አስመራን እንደተቆጣጠረ ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ ብዙ ኢትዮጵያውያንን ከኤርትራ አባረረ፡፡ አንዳንዱ ባዶ እግሩን ነበር የተባረረው፡፡

7. በረፈረንደሙ ጊዜ ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ ምርጫውን ጨርሶ ማኒኪያዊ አደረገው፡፡ ሂደቱን ምርጫው በነጻነትና በባርነት መሃከል መሆኑን በሚያሳምን ረገድ አከናወነው፡፡ ባርነትን የሚመርጥ የለም፤ ግማሽ ነጻነት፡ ግማሽ ባርነት ደግሞ የለም፡፡

ከላይ የተመለከቱት አቋሞችና ድርጊቶች ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን ጋር የመቀራረብ መንፈስ እንዳያዳብሩ፡ በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን በኩል ደግሞ ጥላቻ እንዲሰፍን በማድረግ ላይ ሚና የነበራቸው ይመስላል፡፡ እንዲህ በመሳሰሉት አቋሞችና ድርጊቶች ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ የመገንጠል አጀንዳውን ለማሳካት ችለዋል፡፡

## ፯

አሁን ከመፍትሄ ጋር በተያያዘ የመጨረሻውን ነጥብ ልግለጽ፡፡ በኛ ሁኔታ ለመግባባትና ለመተባበር ደህና ሊያግዝ የሚችል አንዳንድ የሳይኮሎጂ እና ሶሶዮሎጂ ሊቃውንት ቅርጽ ያስያዙት **ቪሰራል ፌርሽተህን** (visceral verstehen) የሚባል ጽንሰ-ሃሳብ አለ፡፡ ቪሰራል ማለት ከውስጥ፡ ከልብ የመነጨ፡ እውነተኛ ማለት ነው፡፡ ፌርሽተህን ደግሞ (በጀርመንኛ) መረዳት ማለት ነው፡፡ ቪሰራል ፌርሽተህን እንግዲህ አንድን ሰው ወይም ህዝብ (እንደየሁኔታው) ከልብ መረዳት፡ ችግሩን ሃዘኑንና ስቃዩን መጋራት በጨመረ መልኩ መረዳት ማለት ነው፡፡

እንዲህ ባለ መልክ ለመረዳት ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ፡፡ እነርሱም የዚያ ህዝብ ታሪክና ሁኔታ በደንብ ማወቅ፡ እና በዚያ ህዝብ ላይ የደረሰውን ስቃይ ባመርቂነት ከግምት ውስጥ ማስገባት ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር የህዝቡን እሮሮ ማዳመጥ፡ ራስን በዛ ህዝብ ቦታ በሃሳብ ማስቀመጥ፣ በዐይነ ህሊና በተባለው ህዝብ ቦታ መሆን ማለት ነው፡፡

ይህ በኛ ሁኔታ ጠለቅ ያለ ጣዕም ያለው ትዝብት ነው፡፡ አንድ ተበድያለሁ የሚል ህዝብ ችግሩን የምታውቅለት ብቻ ሳይሆን ስቃዩንም የምትጋራ መሆንህን ሲያይ ባንተ ላይ እምነት ያሳድራል፡፡ ስለፈጸመው በጎ ነገር ስትመሰክርለት ደግሞ መንፈሱ ይጠነክራል፣ በዚያው መጠንም ካንተ ጋር በበለጠ ለመቀራረብና ለመተባበር ዝግጁነቱ ይዳብራል፡፡

ኢትዮጵያውያንንና ኤርትራውያንን በተመለከተ ይህ ምን ማለት ነው? መጀመርያ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን በጥልቀት መተዋወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ኤርትራውያን የራሳቸውም ታሪክ የሆነውን ረጅሙን የኢትዮጵያን ታሪክ ይወቁት፡፡ እንዲህ የመሰለ ዕውቀት የሁለቱን ህዝቦች ወንድማማችነት በግልጽ ስለሚያስገነዝብ፡ አሁን ሁለቱን ህዝቦች ለማቀራረብ ለሚደረገው ጥረት አጅግ ይረዳል፡፡ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በበኩላቸው አስቀድሜ የጠቀስኩትን ኤርትራውያንን ያሰቃየ ታሪክ በደንብ ማጤን ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን በኤርትራውያኑ ላይ የደረሰው (አሁንም እየደረሰ ያለው) ስቃይና ጭቆና በራሳቸው ላይ ሲደርስ ይገምቱ፣ ኤርትራውያንም እንደዚሁ በኢትዮጵያውያን ዜጎችና በኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ ላይ የተፈጸመውን (አሁንም እየተፈጸመ ያለው) በደል በነርሱ ላይ ሲፈጸም በዓይነ ህሊና ያስቡ፡፡

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ የኤርትራና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ቡድኖች የዚህ አይነት መረዳት ተቃራኒ የሆነ መንፈስ የሚያንጸባርቅ አመለካከት ያላቸው መሆኑ ይታያል፡፡ አንዱ ለሌላው ወገን ወይም ህዝብ ስሜትና ሁኔታ ደንታ የሌለው አቋም ይወስዳል፣ እንቅስቃሴዎችም ያደርጋል፡፡

ከአዲስ አባባ መንግስት ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያላቸው ኤርትራዊ ተቃዋሚ ቡድን መሪዎችና ካድሬዎች: ሁሉም አንኳዋን ባይሆኑ: ጥቂቶቹ  የኢትዮጵያን ያገር ውስጥ ፖለቲካ በሚመለከቱ ጉዳዮች አቋም በመውሰድ የኢህአዲግ (በተለይም የህወሃት) ደጋፊዎች መስለው ይታያሉ፣ ናቸውም፡፡ የኤርትራን ነጻነት የሚያውቅና የሚቀበል ህወሃት ብቻ ነው በሚል አመክንዮ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎችን ሲያቋሽሹና ሲያጥላሉ የሰማሉ፡፡ ይህ ትክክል አይደለም፡፡ እነዚህ ተቃዋሚዎች፡ የኢትዮጵያን ያገር ውስጥ ፖለቲካ በተመለከተ በመሰረቱ ገለልተኛ መሆን አለባቸው፡፡ የኢህአዲግ መንግስት ሰብአዊ መብቶችን በሚገስስበት ጊዜ፡ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን በግፍ በሚያስርበት ጊዜ ኤርትራዊ ድርጅቶች ድጋፍ ሲሰጡት ለኢትዮጵያ ህዝብ ብሶት

ምንም ደንታ (ወይም ሃዘኔታ) የላቸውም ማለት ነው፡፡ ይህም ለወደፊት ዕንቅፋት ይፈጥራል፡፡

በኢትዮጵያውያን በኩልም እንደዚሁ ችግር አለ፡፡ ኢህአዲግን *(በተለይ ወያኔን)* እምብዛም ከመጥላት የተነሳ ኢሳያስ አፈወርቅ ሊረዳን ነው ብለው ማመን የፈለጉ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡ አቶ ኢሳያስን እያደነቁም ናቸው፡፡ አንዳንዱማ የአስመራውን አምባገነን ባለፈው ዓመት "*ያመቱ ምርጥ ሰው*" (Man of the Year) ብሎ እስከማሞገስ ዳርሷል፡፡ ህብረተሰቡን ለመግለጽ በሚያስቸግር መጠን እያሰቃየ ያለውን ጨካኝ አምባገነን እንዲህ አድርጎ መካብ ኤርትራውያንን መናቅ ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ ፍጡራን እንዳልሆኑ መቁጠር ነው፡፡ ይህ የኤርትራ ህዝብን የሚያሳዝንና፡ ግንኙነታችንንም የሚጎዳ ትልቅ መሰናክል የሚያስከትል ነው፡፡ *(ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥበበ ሳሙኤል ፈረንጅ በተከታታይ ካሳተማቸው ይህንን አርእስት የሚመለከቱ አንቀጾች የምስማማ መሆኔን መግለጽ እወዳለሁ፡፡)*

ፌዴራላውነትን በተመለከተ በኢትዮጵያውያንም በኤርትራውያንም በኩል ችግሮች አያለሁ፡፡ ከድሮ (ማለት ከ 40ዎቹ አንስቶ) የነበረው የፖለቲካ አመለካከት ችግር አሁንም ገና ያለ ይመስለኛል፡፡ የአጼው መንግስትም ሆነ ደርግ የኤርትራ ጥያቄ ከነበሩት ጠቅላይ ግዛቶች ወይም ክፍለ-ሃገሮች ጉዳይ ወይንም ብሄረ-ሰቦች ጥያቄ የተለየ መሆኑን መቀበል አልተቻላቸውም፡፡ ይህንን ባለመቀበላቸው አላስፈላጊ እርምጃዎችን ወስደው ኪሳራ አደረሱ፡፡ የኢህአዲግ መንግስት (ወይም ህወሃት) ደግሞ ዲሞክራስያዊ ባልሆነ፡ ሁሉንም የፖለቲካ ቡድኖች ባላሳተፈ፡ ለኢትዮጵያ ህዝብም ለውይይት እንኳን ዕድል ባልሰጠ፡ ረፈረንደም ተብዬ ኤርትራን በኢሳያስ አፈወርቅ እንድትገዛ አሳልፎ መስጠቱ የኤርትራ ህዝብን ለማመን ለሚያስቸግር ጉዳት ዳርጓል፡፡

አሁንም ቢሆን ለኢትዮጵያውያን ወንድሞቼ ለመግለጽ የምፈልገው የሁለቱ አገሮች ዝምድና ምን ይሁን የሚለው ጥያቄ የሚመለሰው አስቀድሜ የጠቀስኩትን ታሪክና ችግር በማጤን መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ይህንን ሁሉ ስናገናዝብ በዚሁ ጊዜ መፍትሄው - ማለት ሊኖር የሚችለው ተግባራዊ ዝምድና - (አምናም እንደገለጽኩት) አንዳንድ የፖለቲካ ቅድመ-ሁኔታዎች ከተሟሉ በሁዋላ የሚቋቋም ኮንፌዴሬሽን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ክፍት ኮንፌዴሬሽን ማለቴ ነው፡፡ ክፍት ኮንፌዴሬሽን ማለት ለሁላችን በሚያረካ አኳሃን ከያዝነው በህዝቦቹ ሙሉ ነጻነትና ፈቃድ ወደ ፌዴሬሽን ሊያድግ የሚችል የፖለቲካ ሂደት ማለት ነው፡፡

በአፍሪቃ ቀንድ አገሮች (ማለት በኢትዮጵያ ጂቡቲ ኤርትራ ሱዳንና ሶማሊያ) መሀከል ፌዴሬሽን አሁን ይቋቋም ቢባልም እኔ በበኩሌ እንደ ራዕይ እጅግ ውብ ነው እላለሁ፡፡ ነገር ግን ተግባራዊነት የለውም፡፡ በአፍሪቃ ቀንድ ደረጃም ተግባራዊነት ያለው ኮንፌዴሬሽን ነው፡፡ ይህም የሚጀምረው በኢትዮጵያና ኤርትራ ኮንፌዴሬሽን ነው፡፡

በኤርትራውያን በኩልም ገና ችግር አለ፡፡ በፌዴሬሽንና ኮንፌዴሬሽን መሃከል ያለውን ልዩነት ባለማወቃቸው፡ ኮንፌዴሬሽን የምትለውን ቃል ሲሰሙ ብቻ የሚበረግጉ አሉ፡፡ ከአምናው ኮንፈረንስ በሁዋላ በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ሳይቀር እኔን "አሁንም ገና ፌዴሬሽን ይለናል" ብለው የተሳደቡ ስንት ነበሩ፡፡ ከሳንሆዘ ስብሰባ በሁዋላ: በስዊድን አገር ባንድ አጋጣሚ አንድ ያገሬ ሰው "ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት አይኖረንም፣ ዝምድናችን ከሱዳን ጋር ነው መሆን ያለበት" ብሎ ሽንጡን ገትሮ ነበር የተከራከረኝ፡፡ ለማስረዳት ሞከርኩ፣ እምብዛም የቀናኝ አልመሰለኝም፡፡

የኢትዮጵያና የኤርትራ ልሂቃን (በተለይ ምሁራኖቹ) ልዩ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ከልብ የመረዳት ጸባይ በማሳየት አርአያ መሆን አለባቸው፡፡ ለምሳሌ

የኤርትራ ምሁራን ኤርትራ ተበድላ፡ ተጨቁና ነበር የሚለውን ስሞታ አሳንሰው፡ ኤርትራ በነበሩት ኢተዮጵያውያን ዜጎች ላይ ከ1991 በሁዋላ ግፍ እንደተፈጸመ፣ እንዲሁም ኤርትራውያን በኢትዮጵያ ተከብረው ይኖሩ እንደነበር፣ ቅኝ ተገዢዎች ሳይሆኑ ሚኒስትሮች፡ ጀነራሎችና ሌላ መኰንኖች፡ ጠቅላይ ዐቃብያነ ህግ፡ ከበርቴ ባልሞያዎች፡ የተሳካላቸው ነጋዴዎች ወዘተ. እንደነበሩ ባአትኩሮት በየጊዜው መመስከር አለባቸው፡፡ ኢትዮጵያውያን ልሂቃንም (በተለይ ምሁራኖቹ) በበኩላቸው ኤርትራውያን ጥለውን ሄዱ እያሉ ማጉረምረም ቀንሰው የኤርትራውያኑን ስሞታ እንደሚረዱ ማሳየት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ ኤርትራ በሴራ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛት እንድትሆን መደረጉ፣ ኤርትራውያን የሲቪልና የፖለቲካ መብታቸው ተገፎባቸው እንደተጨቆኑ፣ የረጅም ዘመናት ታሪካችን አንድ ቢሆንም የኤርትራ ጉዳይ ከሌሎቹ ክፍለ-ሃገራት የሚለይበት ገጽታ እንዳለ፣ ኤርትራውያን ኢትዮጵያ ውስጥ ተከብረው፡ ተሹመው፡ ቀንቷቸውና ተሳክቶላቸው ብቻ ሳይሆን፡ እነርሱም ለኢትዮጵያ ዕድገት በሁሉም ረገድ ብዙ እነዳበረከቱ መመስከር ይኖርባቸዋል፡፡

እንዲህ አይነቱ የልሂቃን ሚና ለኢትዮጵያና ኤርትራ ወዳጅነት፡ ለወደፊቱም በሁለቱ አገሮች መሃከል ለሚከሰት ትስስር ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ዳኛቸው አሰፋ፣ ብርቱካን በሁለት የይቅርታ ስያሜዎች መካከል *(አዲስ ነገር፡ የካቲት* 7፡ 2001)

ዘውዴ ረታ፣ *የኤርትራ ጉዳይ 1941 - 1963 (አዲስ አበባ፡ 1998)*

በዕውቀቱ ስዩም፣ *በራሪ ቅጠሎች* (አዲስ አበባ፡ 1996)

የማነ ናግሽ፡ *"ጭቃ ፖለቲካ" ኢትዮመዲያ.ኮም (March 2010()*

አቤ ጉበኛ፡ *አልወለድም*

ታደሰ ቴለ ሳልቫኖ፡ *አይ ምጽዋ (1997)*

Donald N. Levine, *Ethiopia's Missed Chances – 1960, 1974, 1991, 2005 and Now: II An Ethioopian Dilemma: Deep Structures, Wrenching Processes* (Western Michigan University: August 2007), available in the internet at www.ethiopolitics.com/pdfiles/AnEthiopian%20Dilemma_dl_WMU.pdf

Tibebe Samuel Ferenji, "Mr Issaias: The friend of Ethiopia?" (*ethiomedia.com*, February 19, 2010)

Tibebe Samuel Ferenji , "With all due respect", (*ethiomedia.com*, February 24, 2010)

Yacob Haile-Mariam ,"Civility and political discourse in Ethiopia: Time to change guards", (*ethiomedia.com*, December 14, 2009)

John E. Glass, "Visceral Verstehen", *Electronic Journal of Sociology* (2005) (available in the Internet)

*Makonnen Tegegn*. 1997. Walda-Giyorgis. Walda-Yohannes and the Haile Sellassie government. Northeast African Studies 4 (2)

Peter Heinlein,"Senior Politician; Marxist Legacy Haunts Ethiopia", (*nazret.com.* December 16, 2009)